## ዓለም አቀፍዊ የመሠረታዊ ጤና እንክብካቤ ፕሮግራሞች



የሀገራችንን የመሠረታዊ ጤና እንክብካቤ ተሞክሮዎችን በመቀመር ለዝቅተኛ እና መካከለኛ ገቢ ያላቸው ሀገራት የጤና ስርዓታቸውን ለማጠናከር በሚያስችላቸው መንገድ ልምድ  ያካፍላል፣ በተጨማሪም ከነዚህ ሀገራት የተለያዩ ልምዶችን በመቅሰም ለኢትዮጵያ የመሠረታዊ ጤና እንክብካቤ መጠናከር ትለቅ አስተዋፆ ያደርጋል፤ ብሎም ይህ የመልካም ተሞክሮ ልምድ ልውውጥ የዝቅተኛ እና የመካከለኛ ገቢ ያላቸው ሀገራት የጤና ስርዓታቸውን ከማጠናከር ባሻገር የኢትዮጵያን የመሰረታዊ ጤና እንክብካቤ ያዘምናል፡፡

### ዋና ዓላማ

በዓለም አቀፍ ደረጃ የመሠረታዊ ጤና እንክብካቤ አገልግሎት ፕሮግራም አተገባበርአቅምን ማጎልበት፡፡

## ሀገራዊ የመሠረታዊ ጤና እንክብካቤ ፕሮግራሞች



ኢንስቲትዩቱ የኢትዮጵያ ጤና ስርዓትን በማጠናከር ዓለም አቀፋዊ አብነትነቱን እንደያዘ እንዲቀጥል ድጋፍ ከማድረጉም በተጨማሪ እያደገ የሚመጣውን የህዝብ ፍላጎት ለሟሟላት እና ተደራሽ ለማድረግ በሚደረገዉ ሀገራዊ እንቅስቃሴ ሰፊ ሚና ይጫወታል። በሀገር ውስጥ ያሉትን የጤና አመራሮች የለውጥ መሳሪያዎች እንዲሆኑ እና የዘርፉን ግቦች ለማሳካት እንዲችሉ ተከታታይ የሆነ የብቃት ማጎሌበቻ ፕሮግራሞችን በመንደፍ ኢንስቲትዩቱ ይተገብራል። በተጨማሪም መሠረታዊ ጤና አገልግሎት አሰጣጥን ለማዘመን፣ ተደራሽ እና የተሻሻለ እንዲሆን ለማድረግ፣ የልህቀትና የሰርቶ ማሳያ ማዕከላትን ያቋቁማል፤ አዳዲስ አሰራሮችን/ሃሳቦችን በሙከራ ሂደት እንዲያልፍ ያደርጋል፤ ውጤታማ የሆኑ ዘዴዎችን በመለየት በሰፊው እንዲተገበሩ ያግዛል።

### ዋና ዓላማ

በኢትዮጵያ በመሠረታዊ ጤና እንክብካቤ ዙሪያ የአመራር ብቃት በማጎልበት ፤መረጃ በማመንጨት፤ በምርምር እና በማስረጃ የተድገፈ አሰራር በመንድፍ እና በማካፈል በኢትዮጵያ የጤና ስርዓትን በማጠናከር እንቅስቃሴ ታላቁን ሚና መጫዎት።

## የእውቀት እና የመረጃ አስተዳደርና የክትትል እና የግምገማ ሥርዐት




በመሰረታዊ ጤና አገልግሎት ዙሪያ ምርምሮችን የማካሄደና የፖሊሲ አማራጮችን የማቅረብ አቅምን ማጎልበት፤ የመረጃ ተደራሽነትን መጨመር፤ በመተግበር ላይ ያሉ ፕሮግራሞች ብቃት እና ውጤታማነትን በመገምገም እና ችግሮችን በመለየት የተሻሉ የአሠራር መንገዶችን መጠቆም የኢንስቲትዩቱ ዓላማዎች ናቸዉ። ኢንስቲትዩቱ በመሰረታዊ ጤና አገልግሎት ላይ ምርምሮችን በማካሄደና በሌሎች ተቋማትና፤ግለሰቦች የተሰሩ ሀገርአቀፍና ዓለምአቀፍ ጥናቶችን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በመተንተን እና በመቀመር የፖሊሲ አማራጮችን ያቀርባል። በተጨማሪም በሙከራ የተረጋገጡ አዳዲስ እና ወቅታዊ የአሠራር ሂደቶችና ተሞክሮዎች የሚሠራጩበትን መድረኮች ያዘጋጃል።

### ዋና ዓላማ

የመሠረታዊ ጤና እንክብካቤ ፕሮግራሞች ቀረፃንና ተግባርን ለማጎልበት የእውቀትእና የመረጃ “ቋት” ማደራጀት

## በመሰረታዊ ጤና አገልግሎት ዙሪያ አድቮኬሲ ማካሄድና አጋርነት መፍጠር




በዓለም አቀፍ ደርጃ ሁሉን አቀፍ የጤና ሽፋን በመሠረታዊ ጤና እንክብካቤ አማካኝነት የሚለውን መርህ/ቃል ለማሳካት በሚደረገዉ አድቮኬሲ ኢንስቲትዩቱታላቅ ሚና እየተጫዎተ ይገኛል የጤና አገልግሎቶች በተሻለና ለሕዝቡ ተደራሽ በሚሆን መልኩ ለማደራጀት የሚረዱ ፤ የአመራር ብቃት የሚያጎለብቱ ፤ ለመሠረታዊ ጤና እንክብካቤ ስራዎች ሀገራት በቂ ግብዓት እንዲያሰባስቡ የሚያደርጉ  እና እያደገ የሚመጣውን የህዝብ የጤና ፍላጎት እንዲያሟላ የሚያግዙ የተሻሻሉ ፖሊሲዎችን ተግባራዊነትን ለማሳካት በመሟገት ቁልፍ ሚና ይጫወታል።

### ዋና ዓላማ

በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የመሠረታዊ ጤና ክብካቤ ስርዓት እያደገ የሚመጣውን የህዝብን ፍላጎት ተ  ቁሞ እንዲያሟላ እንዲዳብርና እንዲሻሻል በጥናት የተደገፈ ዉትወታን መደገፍ።